የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፰
አዲስ አበባ – ሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 48
ADDIS ABABA– 22nd April, 1999


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፻፷፯/፲፱፻፺፩ ዓ.ም
የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ .................. ገጽ ፩ሺ፳


## CONTENTS


Proclamation No. 167/1999
Institute of Biodiversity Conservation and Research Establishment (Amendment) Proclamation .... Page 1020


### አዋጅ ቁጥር ፻፷፯/፲፱፻፺፩
### የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፻፷፯/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

፩· በሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፻፳/፲፱፻፺ በአንቀጽ ፲፭ የዱር እንስሳት ጥበቃ ፣ ልማትና አጠቃቀም ድርጅትን የሚመለከተው ተሽሯል ።

፪· የዱር አራዊት ጥበቃና ልማት ባለሥልጣን በዱር አራዊት ጥበቃና ልማት አዋጅ ቁጥር ፻፺፪/፲፱፻፸፪ (እንደተሻሻለ) መሠረት ሥራውን ማከናወኑን ይቀጥላል ።

፫· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

### PROCLAMATION NO. 167/1999
### A PROCLAMATION TO AMEND THE INSTITUTE OF BIODIVERSITY CONSERVATION AND RESEARCH ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Institute of Biodiversity Conservation and Research Establishment Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Institute of Biodiversity Conservation and Research Establishment (Amendment) Proclamation No. 167/1999.''

2. *Amendment*

1/ Article 15 of the Institute of Biodiversity Conservation and Research Etablishment Proclamation No. 120/1998 with respect to Wildlife Conservation and Development Organization is hereby repealed.

2/ The wildlife Conservation and Development Authority shall continue to carry out its functions in accordance with the Wildlife Conservation and Development Proclamation No. 192/1980 (as amended).

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 22nd day of April, 1999.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of April, 1999.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA